ማ ው ጫ

	አንቀጽ	ገጽ
	መግቢያ	1
1.	አጭር ርዕስ	1
2.	የመመሪያው ተፈፃሚነት	1
3.	ትርጓሜ	2
4.	ተግባርና ኃላፊነት	3
5.	ስለ ምዝገባ	4
6.	የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማውጣት	5
7.	ስለሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕድሳት	6
8.	የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማሳደግ	6
9.	ስለድርጅት ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት	6
10.	የድርጅት ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀትን ስለማሳደስ	7
11.	የድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ደረጃን ስለማሳደግ	7
12.	ስለትውልደ ኢትዮጵያዊያን አመልካቾች	8
13.	በዜግነትም ሆነ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ስላልሆኑ ድርጅቶችና ባለሙያዎች	8
14.	ያገልግሎት ክፍያዎች	8
15.	ስለሥራ ልምድ አግባብነትና አያያዝ	9
16.	ስለብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት አሠጣጥና ይዘት	9
17.	የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ስለመተካት	10
18.	ማመልከቻችን ውድቅ ስለማድረግ	10
19.	ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕድሳት	11
20.	የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀትን ስለማገድ	11
21.	ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ .	11
22.	ስለቅሬታ	12
23.	ስለውክልና	12
24.	የሞያ ዝርዝር	13
25.	ስለ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ እና የሞያ ልምድ	13
26.	የውሃ ሥራዎች ማንባታ ሥራ ተቋራጭ የደረጃ ምደባ መሥፈርት	13
27.	የማንባታ ዋጋ መሥፈርት	14
28.	በማንባታ ባለሞያዎች የሞያ ዓይነት የሥራ ልምድ እና ስብጥር ላይ የተመሠረተ መሥፈርት	14
29.	በልዩ ሁኔታ የምሥክር ወረቀት ስለመስጠት	14
30.	ስለአስፈላጊ መሣሪያዎች	15
31.	የውሀ ስራ ተቋራጮች የመሳሪያዎች ምደባ፣ ስለመሳሪያዎች መተካካት	15
32	የአማካሪ ባለሞያዎች የሞያ ዝርዝር	16
33.	ስለባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ እና የሞያ ልምድ	17

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር 1
መዛግብት ቤት
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

አንቀጽ ገጽ

34. የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ የሞያ መስኮች..... 17
35. የአማካሪ ድርጅት ሥራ መሪ ወይም ባለቤት ሆኖ ለመሠማራት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች 18
36. ስለአማካሪ ድርጅቶች ምዝገባ 18
37. የአማካሪ ድርጅቶች የደረጃ አወሳሰን መሥፈርት 18
38. የከተሞች መ. ው. ሳኒቴሽን የአቅም ግንባታ አማካሪነት ዝቅተኛ መሥፈርት..... 19
39. የወረዳ ዋሽ ቡድን አማካሪነት ዝቅተኛ የምዝገባ መሥፈርት 19
40. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ባለሞያዎች ዝርዝር 20
41. ስለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ.. 2o
42. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታ እና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ ምደባ መሥፈርቶች 21
43. የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የግንባታ ዋጋ መሥፈርት 21
44. የጉድጓድ ቁፋሮ የሥራ ተቋራጮች የባለሞያዎች ስብጥር፣ የሥራ ልምድና የሞያ ብቃት መሥፈርት 2ı
45. አስፈላጊ መሣሪያዎች..... 21
46. የውሀ ሳኒታሪ ባለሙያዎች ዝርዝር..... 22
47. የሳኒታሪ ተቋራጭ ደረጃ ምደባ መስፈርቶች..... 22
48. የሳኒታሪ ተቋራጭ የግንባታ ዋጋ መስፈርት..... 22
49. መመሪያውን ስለማሻሻል 22
50. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ 22

ዕዝል

ዕዝል አንድ ሠንጠረዥ 1 የውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ..... 24
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 2 የውሀ ስራ ግንባታ ባለሙያ የስራ ልምድና የሞያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት..... 25
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 3 የውሀ ነክ ስራ ተቋራጭ አስፈላጊ ባለሙያዎች ደረጃ መስፈርት..... 27
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 4 የግንባታ ዋጋን መሠረት ያደረገ የውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት..... 28
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 5 ስለሚተካኩ መሳሪያዎች 29
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 6 ተቋራጮችን በተለያዩ ደረጃዎች የሚያስመድቡ መሳሪያዎች 30
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 7 መሳሪያ ሳይጠየቁ ብቃት ማረጋገጫ የሚሠጣቸው ተቋራጮች 32
ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 8 ለተቋራጮች መሳሪያ ለመከራየት የሚያስችላቸው የዋጋ ግምት 33
ዕዝል ሦስት ሠንጠረዥ 9 የጥናት ዲዛይን እና ቁጥጥር ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ መሥፈርት 35

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ዕዝል ሦስት ሠንጠረዥ 10 የረዥም ጊዜ ባለሙያ መሥፈርት..... 37
ዕዝል ሦስት ሠንጠረዥ 11 የውሃ ሀብት አማካሪ ድርጅትነት ደረጃ መሥፈርት 38
ዕዝል ሦስት ሠንጠረዥ 12 የሃይድሮ ፓወር/የውሃ ኃይል ማመንጫ ምሕንድስና አማካሪ ድርጅትነት መሥፈርት 40
ዕዝል ሦስት ሠንጠረዥ 13 የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ ወይንም/ሳኒተሪ፣ ኤንቫይሮሜን ታል ምሕንድስና አማካሪ ድርጅትነት መሥፈርት 42
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 14 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታ እና ጠረጋ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ 44
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 15 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ/ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ መሥፈርት በግንባታ ዋጋ 46
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 16 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጮች ሊያሟሉ የሚገባቸው አነስተኛ የባለሞያ ፍላጎቶች 46
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 17 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ የባለሞያ የደረጃ ምደባ መሥፈርት 47
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 18 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ ምዘና መሥፈርት በመሣሪያ ዓይነት፣ አቅምና ብዛት 48
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 19 የመቆፈሪያ መሳሪያና የደረጃ አወሳሰን 49
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 20 የመቆፈሪያ መሳሪያ ተጓዳኝ ዕቃዎች 50
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 21 የመቆፈሪያ መሳሪያ መገጣጠሚያዎች 51
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 22 ለውሀ ጉደጓድ ቁፋሮ የሚያስፈልጉ ሌሎች ካፒታል ዕቃዎች 52
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 23 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ተቋራጭ የመሣሪያዎች ባለቤት ካልሆነ መሣሪያዎቹን በኪራይ ለማግኘት የሚያስችለው የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጫ መሥፈርት 54
ዕዝል አራት ሠንጠረዥ 24 የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅት ለብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርበው መሳሪያ ብዛት 55
ዕዝል አምስት ሠንጠረዥ 25 ለሣኒተሪ ተቋራጭ የሚያስፈልጉ ባለሙያዎች የት/ደረጃና የሥራ ልምድ.....56
ዕዝል አምስት ሠንጠረዥ 26 መሳሪያ ሳይጠየቁ የሳኒታሪ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው
ዕዝል አምስት ሰንጠረዥ 27 የውሃ ሳኒታሪ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የግንባታ ዋጋ መሥፈርት.....57
ዕዝል ስድስት ሰንጠረዥ 28 ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚከፈል የክፍያ መጠን በብር.....57

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
ሠነድ ቤተ
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

የውሃ ነክ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሞያዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ

መግቢያ

የውሃ ነክ ሥራ ጥናት፣ ዲዛይን፣ ግንባታና ቁጥጥር በዘርፉ የሰለጠነ ባለሙያ፣ መሣሪያና ካፒታል የሚጠይቅ የሥራ መስክ ከመሆኑም በላይ የውሃ ሀብቶችን ለልማት እንዲውል በማስቻል ረገድ ለአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፣

በውሃ ነክ ሥራዎች የሚሰማሩ ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም በመስኩ የተሰማሩ፣ ተቋራጭና አማካሪ ድርጅቶች በቂ የባለሙያ ስብጥርና ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል አስፈላጊ መሳሪያዎች ያላቸው ወይም ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ማረጋገጥ የህዝብንና የመንግሥትን ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፣

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በዘርፉ የተሰማሩትን ባለሙያዎች፣ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች ከሥራ ጥራትና ብቃት አንፃር መቆጣጠር የሚያስችል መመዘኛ መስፈርት መኖር ያለበት በመሆኑ፣

የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 በአንቀፅ 31 እና በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ደንብ ቁጥር 115/1997 አንቀፅ 20 እና 21 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የውሃ ነክ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና ባለሙያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በሚመለከት የወጣ መመሪያ ቁጥር ውመኤሚ 1/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ ተቋራጮች እና የማማከር ሥራ ላይ በሚሠማሩ ድርጅቶችና ባለሙያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው::
2. "ዳይሬክቶሬት" ማለት በሚኒስቴሩ የውሃ አጠቃቀም ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ነው::
3. "ዳይሬክተር" ማለት የዳይሬክቶሬቱ መሪ ነው::
4. "አመልካች" ማለት በውሃ ነክ ሥራ ባለሙያነት፣ በአማካሪ ወይም ሥራ ተቋራጭነት ለመመዘገብ ያመለከተ ሰው ነው::
5. "ባለሞያ" ማለት የውሃ ነክ ሥራዎች ጥናት ዲዛይን ቁጥጥር ወይም ግንባታ ባለሞያ ነው::
6. "ሥራ ተቋራጭ" ማለት የውሃ ነክ ሥራ ግንባታ ስራን በክፍያ ለማከናወን የተቋቋመ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የግልም ሆነ የመንግሥት ድርጅት ነው::
7. "አማካሪ" ማለት የውሀ ነክ ስራ ጥናትን፣ ዲዛይንንና ቁጥጥር ተግባራትን በክፍያ ለማከናወን የተቋቋመ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የግልም ሆነ የመንግሥት ድርጅት ነው::
8. "ድርጅት" ማለት በሥራ ተቋራጭነት ወይም በአማካሪነት የውሃ ነክ ሥራ ጥናት፣ ዲዛይን፣ ቁጥጥር ወይም የግንባታ ተግባራትን በክፍያ ለማከናወን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ደርጅት ነው::
9. «የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት» ማለት የባለሙያን፣ የስራ ተቋራጭንና የአማካሪን ብቃት በማረጋገጥ በሚኒስቴሩ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው::
10. «መዝገብ» ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በውሃ ሥራ ተቋራጭነት፣በአማካሪነት፣በባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሰዎችን ዝርዝር የሚይዝ ቋት ነው::
11. «ውሃ ነክ ሥራ» ማለት የውሃ ሀብትን ጠቀሜታ ላለው ተግባር ለማዋል የሚከናወኑና የሚገነቡ ማናቸውም ሰው ሰራሽ ሥራዎች ሲሆኑ ይህም ጥናትን፣ ዲዛይንን፣ ቁጥጥርን፣ መጥለፍን፣ መገደብን፣ መመርመርን፣ መቆጣጠርን፣ ማጣራትን፣ መለካትን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን፣ ጨው አልባ ማድረግን፣ ጎርፍ መከላከያ መገንባትን፣ ውሀ ጉድጓድ መቆፈርን መጥረግንና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወንን ያጠቃልላል::
12. «የውሀ ጉድጓድ» ማለት በእጅ ከሚቆፈሩ ጉድጓዶች በስተቀር ለተለያዩ አገልግሎቶች የተለያዩ መሳሪያዎችን /ሪግ/ በመጠቀም የከርሰምድር ውሀ አመንጪ ወይንም አስተላላፊ አካሎችን ለመዝለቅ የሚቆፈር ጉድጓድ ነው::
13. «የውሀ ጉድጓድ ጠረጋ» ማለት የውሀ ጉድጓድ አመንጪ መስመሮች በአሸዋ በመሞላታቸው፣ ስንጥቅ ቀፎዎች በተለያዩ ንጥረ ነገሮች በመደፈናቸው ወይም በኬሚካል አክሽን በመዘጋታቸው

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ወዘተ... የተነሳ ውሀ የማመንጨት ሀይሉን ወይም ችሎታውን የቀነሰ የውሀ ጉድጓድን የውሀ የማመንጨት ሃይል ለማሻሻል ሲባል ሙያው በሚጠይቀው ዘዴ በተለያዩ መሳሪያዎች በመጠቀም የሚከናወን ስራ ነው::

14. «አዋጅ» ወይም ደንብ» ማለት አንደ ቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 ወይም ደንብ ቁጥር 115/1997 ነው::
15. "መሰየም" ማለት በኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ መሠረት በወንጀል የተቀጣ ሰው ከመቀጣቱ በፊት የነበረው ንፁህ ስም አግባብነት ባለው ፍ/ቤት የተመለሰለትና ተወስኖበት የነበረው ፍርድም የተሰረዘለት ነው::
16. "የሣኒቴሪ ተቋራጭ" ማለት ከውሃ ጋር የተያያዙ ፍላሾች የሚወገዱበትን ሥራ የሚሰራ ድርጅት ነው::
17. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብትና ግዴታ የተሰጠው አካል ነው::

ክፍል ሁለት
የዳይሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነት

4. ተግባርና ሀላፊነት

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት፣ለማደስ ወይም ለማሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይቀበላል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት የቀረቡ ማመልከቻዎች አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው በሚያዘው መሠረት በመረጃ ተሟልተው መቅረባቸውንና ትክክለኛ መሆናቸውን በማረጋገጥ አመልካቹ እንዲመዘገብ፣ የምስክር ወረቀቱ እንዲታደስ፣ እንዲሻሻል ወይም ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ይወስናል፤
3. የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት እንዲሰረዝ ወይም በሌላ እንዲተካ የቀረበ ማመልከቻን በመመርመር ይወስናል::
4. የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በሥራ አፈጻጸሙ ሞያው የሚጠይቀው ብቃት የሌለው ወይም ተግባሩን በአግባቡ ያልተወጣ መሆኑን በተግባር ሲያረጋግጥ የምስክር ወረቀቱን ያግዳል ወይም ይሰርዛል::

Archive

ክፍል ሦስት

ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

5. ስለ ማመልከቻ

1. በአዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያ የተመለከቱ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያሟላ ባለሞያ፣ የሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻም ለዚሁ ተግባር እንዲውል በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ ቅጽ መሠረት መሆን አለበት።

3. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው የነበሩ ባለሙያዎች፣ አማካሪ ድርጅቶችና ሥራ ተቋራጮች በዚህ መመሪያ መሠረት እንደ አዲስ መመዝገብ አያስፈልጋቸውም። ሆኖም ለዕድሳት ሲመጡ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

4. ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ በውሃ ነክ ስራ ተቋራጭነት ለመሰማራት የሚፈልግ የውጭ ተወላጅ በዚህ መመሪያ መሠረት መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ ለብቻውም ሆነ ከኢትዮጵያዊ/ያን ጋር ተቀናጅቶ ቢመጣ ሊመዘገብ የሚችለው በአንደኛ ደረጃ ሥራ ተቋራጭነት ብቻ ነው። ሆኖም የውጪ ተወላጆች የሚያቋቁሙዋቸው አማካሪ ድርጅቶች የደረጃ ወሰን የለባቸውም።

5. በዚህ መመሪያ መሠረት በውሃ ነክ ሥራ ተቋራጭነት የተመዘገበ ድርጅት በድጋሚ በአማካሪ ድርጅትነት ለመሠማራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያወጣ አይችልም። እንዲሁም በአማካሪ ድርጅትነት የተመዘገበ ድርጅት በውሃ ነክ ሥራ ተቋራጭነት ለመሠማራት የሚያስችል የምስክር ወረቀት ሊያወጣ አይችልም። ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሁለቱም ዘርፎች ፈቃድ ያወጣ ድርጅት ካለ አንዱን ፈቃድ መርጦ ለፈቃድ ሰጪው አካል መመለስ ይኖርበታል።

6. ማንኛውም ስሙ በመዝገብ የሰፈረ ሰው በማመልከቻው ውስጥ የተመለከቱ በየጊዜው የተደረጉ የለውጥ ሁኔታዎች እንዲመዘገቡለት ለዳይሬክቶሬቱ ማሳወቅ ይችላል። ዳይሬክቶሬቱም በዚሁ መሠረት የተደረጉ ለውጦችን በመመዝገብ መዝገቡን ወቅታዊ ያደርጋል።

7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና የዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፦

   ሀ. አንድ ባለሞያ በመጀመሪያ የተሰጠውን ብቃት ማረጋገጫ ወደ ሌላ ዓይነት ብቃት ማረጋገጫ ለመቀየር ቢፈልግ ሊቀየር የሚችለው የመጀመሪያን የብቃት ማረጋገጫ ካወጣበት ቀን ጀምሮ ከ3 ወር በኋላ ይሆናል።

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ለ. በውሃ ነክ ሥራ ተቋራጭነት ወይም አማካሪ ድርጅትነት ለመሰማራት የብቃት ማረጋጫ የምሥክር ወረቀት ያወጣ ሰው የምስክር ወረቀቱን ደረጃ ለመለወጥ የሚችለው የቀድሞውን ከወሰደ ከ3 ወር በኋላ ይሆናል።

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከቱት ተፈፃሚ የሚሆኑት አመልካቾች ጥያቄያቸውን በጽሁፍ ሲያቀርቡ ብቻ ነው።

6. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

1. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚፈልግ ሰው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት።

ሀ. ለዘመኑ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርትና አድራሻ የሚያሳይ ሌላ ማንኛውም የታደሰ መታወቂያ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

ለ. ኦሪጅናል ወይም ጊዜያዊ ዋና የትምህርት ማስረጃ ከአንድ አንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

ሐ. በውሃ ነክ ሥራ ላይ መስራቱን የሚያረጋግጥ የሥራ ልምድ ካለ ኦሪጂናል ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

መ. 3x4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ነ/ሀ/ ፪ መሰረት የቀረበው የትምህርት ማስረጃ ከውጭ ሀገር የትምህርት ተቋም የተገኘና ቀደም ሲል የአቻ ግምትን አስመልክቶ ትምህርት ሚኒስቴር ባስተላለፈው ተቋማት ዝርዝር ውስጥ ካልተካተተ በሚኒስቴሩ የተሰጠ የአቻ ግምት ማስረጃ ከፎቶ ኮፒው ጋር መቅረብ አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ነ/ሀ/ ፪ መሰረት የቀረበው የትምህርት ማስረጃ ጊዜያዊ ከሆነና ከተሰጠ ሁለት ዓመት ካለፈው አመልካቹ አርጅናል የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ አለበት። ሆኖም አርጅናሉ የትምህርት ማስረጃ ሊቀርብ ካልቻለ አርጅናሉ ለአመልካቹ አለመሰጠቱን የሚያረጋግጥ ከተቋሙ የተሰጠ የጽሁፍ ማስረጃ መቅረብ አለበት።ይህም በሌለ ጊዜ በቀረበው ጊዜያዊ የትምህርት ማስረጃ ጀርባ ላይ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጥ የተቋሙ ማህተም የታተመበት ወይም አመልካቹ ከተቋሙ ጋር የገባውን የወጪ መጋራት በተመለከተ የገባውን ውል ማቅረብ አለበት።

4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የሞያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ሲጠይቁ በአዋጅ ቁጥር 351/95 መሰረት ከሚሰሩበት ተቋም መልቀቂያ እንዲያቀርቡ ሳይጠየቁ ማግኘት ይችላሉ።

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

7. ስለሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕድሳት

1. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በደንቡ አንቀጽ 25/1 መሰረት በማንባር ቀርቦ መታደስ አለበት::
2. ለዕድሳት የቀረበው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሁለት ዓመት በፊት የተሰጠ እና የተሰጠውም በጊዜያዊ የትምህርት ማስረጃ ከሆነ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/1/ሀ/ፎ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል::

8. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ደረጃን ስለማሳደግ

1. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ደረጃን ለማሳደግ የሚፈልግ ሰው ሚኒስቴሩ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅጽ መመላትና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሟላት አለበት::

   ሀ. የቀድሞ የብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት አሪጅናል

   ለ. ደረጃውን ለማሳደግ በማስረጃነት ሊቀርቡ የሚገቡ ሰነዶች አሪጅናልና ፎቶ ኮፒ

   ሐ.3x4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ በማንባር መቅረብ አለበት

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ መሰረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ደረጃ ለማሳደግ ያመለከተ ሰው የቀድሞ የምስክር ወረቀት የተሰጠው በጊዜያዊ የትምህርት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ከነበረ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/1/ሀ/ፎ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

9. ስለድጋፎት ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት

1. የድጋፎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚፈልግ ሰው ሚኒስቴሩ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት:-

   ሀ. ማመልከቻውን ያቀረበው ባለሙያ ከሆነ ለዘመኑ የታደሰ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

   ለ. ለዘመኑ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ከፎቶ ኮፒ ጋር፣

   ሐ. አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ ህጋዊ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ

   መ. አመልካች የንግድ ማህበር ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃ

   ሠ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /Tin Number/፣

   ረ. በዚህ መመሪያ መሠረት ለየደረጃው የተጠየቁ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ለዘመኑ የታደሠ የባለቤትነት ማስረጃ፣

   ሰ. መሳሪያዎቹን ወይም ዕቃዎቹን በኪራይ ለመሟላት የቀረበ ጥያቄ ከሆነ በዚህ መመሪያ ዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ ስምንት ወይም እዝል አራት ሠንጠረዥ 23 የተወሰነ የገንዘብ መጠን ለመኖሩ የሚያረጋግጥ 15 ቀናት ያላለፈው ከባንክ የተሰጠ ደብዳቤ

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ሸ. በዚህ መመሪያ መሠረት ለተጠየቀው ደረጃ መሟላት ያለበት ባለሞያ ከቅጥር ፣ ስምምነት ጋር

ቀ. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ <<ሸ>> መሠረት ለተጠየቀው ደረጃ የቀረበው ባለ፣ ከሌላ ድርጅት ዝውውር ሊያደርግ ከሆነ ከቀድሞ አሰሪው የተሰጠ የስራ መልቀቂያ

በ. ድርጅቱ መስሪያ ቦታ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃ ካርታ ወ የኪራይ ከሆነ ውለታን ለማጽደቅ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የቤት ኪራይ ፣ አሪጅናልና ኮፒ

ተ. የድርጅቱ ባለቤት ወይም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ 3x4 የሆነ ፎቶ ግራፍ::

2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ማመልከቻ ያቀረበው የድርጅቱ ባለቤት፣ አስኪያጅ ወይም ሕጋዊ ውክልና የተሰጠው ሰው በግንባር መቅረብ አለበት::

10. <u>የድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕድሳት</u>

1. የድርጅት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟ ይኖርባቸዋል

ሀ. ለዚሁ ተግባር በሚኒስቴሩ የተዘጋጀ ቅጽ በድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጅ ወይም ሀ ውክልና ማስረጃ ባለው ሰው ተሞልቶና ተፈርሞ ከውክልናው ፎቶ ኮፒ ጋር፣

ለ. የድርጅቱ ባለሙያዎች ለዘመኑ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሁለት ኮፒ ጋር፣

ሐ. በቅጹ ላይ የተሞሉ ባለሙያዎች ቀድሞውኑ የነበሩ ወይም አዲስ ምሩቃን ካልሆኑ በስተ ከቀድሞ አሰሪያቸው የተሰጠ የሥራ መልቀቂያ፣

መ. ባለሙያዎቹ የድርጅቱ ነባር ተቀጣሪ ከሆኑ በተከታታይ የሶስት ወር ደመወዝ የተከፈለበት ኮፒ፣

2. አመልካቹ ድርጅት ቀደም ሲል መመሪያው በሚጠይቀው መሰረት ለደረጃው መሟላት ያለበት ፣ ወይም መሳሪያ ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ በድጋሚ እንዲያቀርብ አይጠየቅም::

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ድርጅቱ ቀድሞ አስመዝግቧቸው የነበሩ ዕቃዎ ወይም መሳሪያዎች የሌሉት መሆኑ ከተረጋገጠ መመሪያው በሚጠይቀው መሰረት ይህንኑ ማሟ አለበት::

11. የድርጅት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት <u>ደረጃን ስለማሳደግ</u>

የምሥክር ወረቀት ደረጃ ለማሳደግ የሚቀርብ ጥያቄ በሚኒስቴሩ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ተሞልቶ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት::

1. ለተጠየቀው ደረጃ በመመሪያው መሠረት እንዲሟሉ የሚፈለጉ ዕቃዎች ወይም መሳሪያዎ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ለዘመኑ የታደሠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ዕቃዎቹንና መሳሪያዎች በኪራይ ለማግኘት የሚያስችል ገንዘብ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ከተሰጠ 15 ቀናት ያላለፈ ከባንክ የተሰጠ የጽሁፍ ማስረጃ ፣

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

2. ለተጠየቀው ደረጃ በመመሪያው መሠረት ማሟላት ያለበት የመሥሪያ ቦታ መኖሩን የሚያረጋግጥ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የቤት ኪራይ ውል፣

3. በመመሪያው መሠረት ለተጠየቀው ደረጃ እንዲሟሉ የሚፈለጉ ባለሙያዎች ከዘመኑ የታደሠ የብቃት ማረጋገጫ አሪጅናል ከሁለት ፎቶ ኮፒ ጋር፣

12. ስለትውልደ ኢትዮጵያዊያን አመልካቾች

1. የድርጅት ብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ጥያቄ የቀረበው በትውልደ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሌላ አገር ዜግነት በያዘ አመልካች ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ላይ ከተዘረዘሩት መረጃዎች በተጨማሪ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ መታወቂያ መቅረብ አለበት::

2. በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጪ ዜግነት ያላቸው ተቀጣሪ ባለሙያዎች ደረጃ ለማሳደግና ለማደስ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የስራ ፈቃድ እንዲሁም በአንቀጽ 6.1.ለ መሰረት የትምህርት አቻ ግምት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው::

13. በዜግነትም ሆነ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ያላልሆኑ ድርጅቶች ወይም ባለሙያዎች

1. በዜግነትም ሆነ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚኒስቴሩ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይዙ በውሀ ነክ ስራ ሊሰማሩ አይችሉም::
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ከተመለከቱት ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው::
   ሀ. ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሪጅናልና ኮፒ
   ለ. ለባለሙያዎቹ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የስራ ፈቃድ

3. በዜግነትም ሆነ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ሰዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የስራ ፈቃድ ማቅረብ አለባቸው::
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሠረት የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያመለከቱ ሰዎች ማሟላት የሚገባቸው የትምህርት ደረጃ የሚጠይቀው ከመጀመሪያ ዲግሪ በታች ከሆነ በውጪ አገር የተገኘ የትምህርት ማስረጃ አቻ ግምት እንዲያቀርቡ አይጠየቁም::

14. ያገልግሎት ክፍያዎች

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች በዚህ መመሪያ በዕዝል 6 ሠንጠረዥ 28 ላይ በተመለከተው መሠረት ይሆናል::
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ደረጃ ለማሳደግ የቀረበው ጥያቄ የዕድሳት ዘመን ከመድረሱ በፊት ከሆነ የሚከፈለው ክፍያ ደረጃ ለማሳደግ የሚከፈልን ብቻ ይሆናል::
3. የእድሳት ወቅት ሳያሳልፍ የባለሙያ ብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት ወደሌላ ሙያ ብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት ለመቀየር የሚቀርብ ሰው የሚከፍለው ክፍያ ለአዲሱ የሞያ መስክ ይሆናል::

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

15. ስለሥራ ልምድ አግባብነትና አያያዝ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የባለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለበት የስራ ልምድ አግባብነትና አያያዝ እንደሚከተለው ነው::

   ሀ/ ለመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ ላሉ የትምህርት ደረጃዎች የሚቀርብ የሥራ ልምድ ከምረቃ በኋላ የተገኘ መሆን አለበት:: ሆኖም በመጀመሪያ ዲግሪ የተገኘ የሥራ ልምድ ተያያዥነት ላለው ሞያ ለ2ኛና 3ኛ ዲግሪም የሚያዝ ይሆናል:: እንዲሁም በዲፕሎማና በአድቫንስ ዲፕሎማ የተገኘ የሥራ ልምድ ለተያያዥ ሞያ የመጀመሪያ ዲግሪ ከተገኘ በኋላ ለሚጠየቅ የሥራ ልምድ የሚያዝ ይሆናል::

   ለ/ ቀደም ሲል እውቅና ካለው ተቋም ስድስት ወርና ከዚያ በላይ በተሰጠ ስልጠና/ትምህርት ከተገኘ ሠርተፊኬት በኋላ የተገኘ የሥራ ልምድ ለዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ ለሚጠየቁ የሞያ ልምድ የሚያዝ ይሆናል::

   ሐ/ ቀደም ሲል ሕጋዊ ሰውነት ከተሰጠው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ካልሆነ ተቋም/ድርጅት/ ያለሥልጠና በልምድ ብቻ የተገኘ የስራ ልምድ ከዲፕሎማ በታች በተገኘ የትምህርት ደረጃ ለሚሰጡ የፈቃድ ዓይነቶች ለሚጠየቁ የሥራ ልምዶች የሚያዝ ይሆናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት የሚጠየቁ የሥራ ልምድ ማስረጃዎች የተሰጡት ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ካልሆኑ ማስረጃዎቹ የሚያዙት አመልካቹ ለሠራባቸው ጊዜያት ተገቢው የሥራ ግብር በአግባቡ የተከፈለ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማስረጃ ከአሰሪው ከተሰጠ ብቻ ነው::

3. አመልካች የራሱን ድርጅት አቋቁሞ ሲሰራ የነበረ ከሆነ ልምድ የሚያዝለት ድርጅቱን ከመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የሰራውን ስራና የጊዜ ርዝመት የሚያሳዩ የስራ ስምምነቶችና ከአሰሪዎች የተሰጡ ማስረጃዎች በማቅረብ ይሆናል::

16. ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ይዘት

1. አዋጁ፣ ደንቡና ይህ መመሪያ የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች ያሟላ ባለሞያ፣ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ድርጅት ስሙ በመዝገብ የመግባት መብቱ እንደጠበቀ ሆኖ እንደአግባቡ የብቃት ማረጋጫ ወይም የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል::

2. ከአንድ የትምህርት ዓይነት በላይ ተምሮ ሁለት ዲግሪ ወይም ሁለት ማስተርስ ወይም ሁለት ዶክትሬት ካልኖረው በአንድ ዓይነት የትምህርት መስክ ብቻ የተመረቀና ወደ ማንኛውም የትምህርት

Archive
Ministry of Water, Irrigation

ደረጃ የደረሰ ባለሙያ በተለያዩ ዓይነት ሥራዎች ልምድ ቢኖረውም ከአንድ በላይ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማውጣት አይችልም::

3. በሚኒስቴሩ የሚሰጥ የሞያ ብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት እንደአግባቡ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት:-

ሀ. የባለሞያውን/የድርጅቱን ሙሉ ስም፣
ለ. የሥራ ቦታ አድራሻን፣
ሐ. የምስክር ወረቀቱን ደረጃና ስያሜ /መጠሪያ/፣
መ. የተሰጠበትን ቀን፣መለያ ቁጥር
ሠ. ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ፣
ረ. በተከታታይ እንደሁኔታው የታደሰበትን ቀን፣
ሰ. የምስክር ወረቀት ያዣን ፎቶግራፍ፣
ሸ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
ቀ. የሰጪውን ሥም፣ ፊርማና የሚኒስቴሩን ማኅተም፣

17. የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀትን ስለመተካት

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ሰው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟላ ምትክ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል::

1. የምስክር ወረቀቱ የጠፋ ወይም የተበላሸ መሆኑን በማንባር ቀርቦ ለዚሁ የተዘጋጀ ቅጽ ከሞላ
2. የምስክር ወረቀቱ ስለመጥፋቱ ከፖሊስ የተሰጠ ማስረጃ ሲያቀርብ
3. የምስክር ወረቀቱ የተበላሸ መሆኑ በማንባር አቅርቦ መበላሸቱ ሲረጋገጥ
4. በምትክ ተፈጻሚ ለሚሆነው የምስክር ወረቀት ክፍያ ሲከፍል

18. ማመልከቻን ውድቅ ስለማድረግ

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የቀረበ ማመልከቻ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ውድቅ ሊደረግ ይችላል:: ይኸውም አመልካቹ:-

1. ከታወቀ የህክምና ተቋም የአዕምሮ ችግር ያለበት ስለመሆኑ የተወሰነና ለዚህም የጽሑፍ ማስረጃ የቀረበበት ከሆነ፣

Archive
Ministry of Water, Irrigation

2. አግባብነት ባለው ፍ/ቤት የመሰየም ውሳኔ የተሰጠው ስመሆኑ ማስረጃ ካሳቀረበ በስተቀር በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማጭበርበር ወይም ዕምነት በማጉደል ወንጀል የተፈረደበት ከሆነ፣
3. በእካሉ ላይ ባለ ችግር ምክንያት ብቃት ማረጋገጫ የተጠየቀበትን ተግባር ለማከናወን እንደማይችል አግባብ ባለው የሕክምና ተቋም ተረጋግጦ ማስረጃ የቀረበበት ከሆነ፣
4. በአዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉ አስፈላጊ ሁኔታዎችን የማያሟላ ከሆነ።
5. የብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ያቀረበው ማስረጃ ወይም መረጃ ሀሰተኛ ከሆነ

19. ስለብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት ዕድሳት

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በደንቡ አንቀጽ 21/2/ ላይ በተደነገገው መሠረት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየዓመቱ ቀርቦ መታደስ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያልታደሰ የሞያ ፍቃድም ሆነ የምስክር ወረቀት ሊታደስ የሚችለው በየዓመቱ መክፈል ካለበት የአገልግሎት ዋጋ ላይ እንደቅደም ተከተሉ 10% እና 20% ቅጣት ታክሎበት ይሆናል።

20. <u>የብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ</u>

1. የብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ሊረጋገጥ ይችላል፡-
   ሀ. በሚኒስቴሩ እንዲቀርቡ የተጠየቁ ሪፖርቶች፣ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች ካልቀረቡ፣
   ለ. ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሞያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር በመጣስ ስራውን ተገቢባልሆነ አሠራር ያከናወነ ስለመሆኑ ከተጠቃሚዎች ቅሬታ ሲቀርብና ሲረጋገጥ
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት በምስክር ወረቀት ያዡ ላይ የተወሰደ የዕገዳ ርምጃ የሚቆየው ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ ከሀ-ለ በተጠቀሱት ጉድለቶች ምክንያት የተጣለ እገዳ የሚነሳው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መስተካከሉ ሲረጋገጥ ይሆናል።
4. የምስክር ወረቀትን ያሳገዱ ምክንያቶች እገዳው በተጣለ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካልተስተካከሉ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል።

21. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለመሠረዝ</u>

የብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል። ይኸውም፡-

1. ባለሙያው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣

Archive
Ministry of Water, Irrigation

2. በባለሞያው ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ወይም የማይመለከተው ሰው እንዲጠቀምበት ሰጥቶ ከሆነ፤
3. ድርጅት መክሰሩ ወይም መፍረሱ አግባብነት ባለው ፍ/ቤት ሲረጋገጥ ወይም በራሱ ምክንያት ሥራውን አቁሞ የምሥክር ወረቀቱን ሲመልስ፤

22. ስለቅሬታ

1. የምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ለማሳደስ ወይም ለማሻሻል የቀረበ ማመልከቻ በብቃት አረጋጋጩ ባለሞያ ውድቅ በመደረጉ ወይም በመሠረዙ ወይም በመታገዱ ወይም አይሻሻልም በመባሉ ወይም በማናቸውም ምክንያት ማመልከቻው ውድቅ በመደረጉ ቅር የተሰኘ አመልካች የቅሬታው ምክንያት ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዳይሬክተሩ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ቅሬታ የቀረበለት ዳይሬክተርም የቀረበው ቅሬታ በመመርመር ውሳኔውን በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/2/ መሠረት የዳይሬክተሩ ውሳኔ የደረሰው አመልከች በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊ ቅሬታውን በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል::

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/3/ መሠረት ቅሬታ የቀረበለት የመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊም የቀረበውን ቅሬታ በመመርመር ውሳኔውን በ15 ቀናት ውስጥ ለአመልከቹ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት::

5. የመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች በአዋጁና በደንቡ መሠረት ቅሬታውን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው የፍትህ አካል ማቅረብ ይችላል::

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ና 3 ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ያላቀረበ አመልካች ቅሬታው ተቀባይነት አይኖረውም:: ሆኖም ቅሬታውን ሊያቀርብ ያልቻለው በኢትዮጵያ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 1793 ከ ሀ-ሠ በተጠቀሰው መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ሀይል ምክንያት መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ ማመልከቻው ተቀባይነት ይኖረዋል::

23. ስለ ውክልና

1. የሞያ ብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት፤ ለማደስ፤ ደረጃ ለማሳደግ ወይም ምትክ ለመውሰድ የሚፈልግ ሰው ጉዳዩን በውክልና ሊያስፈጽም አይችልም::

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

2. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የሚፈልግ ባለሙያ በአካል መቅረብ አለበት::

3. የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲታደስለት የሚፈልግ በአካል መቅረብ ካልቻለ ስልጣን ባለው አካል ከተሰጠ 6 ወር ያላለፈው የውክልና ስልጣን ማስረጃ መሠረት ሊያሳድስ ይችላል::

4. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ቢኖርም የድርጅት የብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀትን ለማሳደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር ተያይዞ ከቀረበ የድርጅቱ ነባር ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማሳደስን በተመለከተ ተፈጻሚ አይሆንም

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ድርጅቱ የባለሙያዎቹን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያሳድስ የሚችለው ቢያንስ ላለፉት ሶስት ወራት የባለሙያዎች ደመወዝ የከፈለበት ኦሪጂናል ማስረጃ እና ኮፒ ሲያቀርብ ይሆናል::

ክፍል አራት

ስለውሃ ነክ ሥራ ባለሙያዎችና የሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርት (የንግድ ምዝገባ ኮድ 5022)

24. የሞያ ዝርዝር

በዚህ መመሪያ መሰረት በውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ የሥራ ዘርፍ የሚሰማራ ባለሞያ በውሃ መሐንዲስነት ማለትም በውሃ ሀብት፣ በሃይድሮሊክስ፣ በመስኖና ድሬኔጅ፣ በውሃ አቅርቦት፣ በሳኒቴሪና ኢንቫይሮመንት፣ በሃይድሮፓወር፣ ሲቪል ኢንጂነር፣ ኤሌክትሮ ሜካኒካል መሃንዲስና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ውሃ ነክ ሙያዎች፣ ምሩቅ መሆን አለበት::

25. ስለ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ እና የሞያ ልምድ

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 24 ላይ የተዘረዘሩት ምሩቅ ባለሞያዎች በዚህ መመሪያ ዕዝል አንድ ሠንጠረዥ አንድ ውስጥ የተመለከተው ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ እና የሞያ ልምድ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል::

26. የውሃ ሥራ ተቋራጭ የደረጃ ምደባ መሥፈርት

1. የውሃ ሥራዎች ግንባታ ሥራ ተቋራጭ አሥር ደረጃዎች ይኖሩታል፣

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

2. የሥራ ተቋራጮች ደረጃ የሚወሰነውም፡-

ሀ. በግንባታ ዋጋ፤

ለ. በባለሞያዎች የሞያ ዓይነት፣ የሥራ ልምድና ብቃት እንዲሁም ስብጥር፤

ሐ. በመሣሪያዎች ዓይነት፣ አቅምና ብዛት ነው።

3. ከደረጃ ሰባት አስከ አስር ያሉ ደረጃዎችን የሚጠይቁ ስራ ተቋራጮች በትምህርት ዝግጅትና ስራ ልምድ በዕዝል 2 ሠንጠረዥ 7 መሠረት ይስተናገዳሉ።

27. የግንባታ ዋጋ መሥፈርት

የግንባታ ዋጋን መሠረት ያደረገ የውሃ ነክ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት በዚህ መመሪያ በዕዝል 2 በተመለከተው ሠንጠረዥ አራት መሠረት ይሆናል።

28. በግንባታ ባለሞያዎች የሙያ ዓይነት፣ የሥራ ልምድና ስብጥር ላይ የተመሠረተ መሥፈርት

1. በባለሞያዎች የሞያ ዓይነት፣ ብዛት፣ የሥራ ልምድና ብቃት እንዲሁም ስብጥር መሠረት ያደረገ የሥራ ተቋራጮች ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት በዚህ መመሪያ በዕዝል 2 ሠንጠረዥ 3 መሠረት ይሆናል።
2. በዚህ መመሪያ በዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ 3 የውሃ ነክ ሥራ ተቋራጭ ባለሞያ የስራ ልምድና የሞያ ብቃት ደረጃ መሥፈርትን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የተጣመሩ ባለሞያዎች እርስ በርስ ሊተካኩ ይችላሉ፣

ሀ. ባለሞያ መሐንዲስ I እና ተባባሪ መሐንዲስ IV

ለ. ባለሞያ መሐንዲስ II እና ተባባሪ መሐንዲስ V

ሐ. ተባባሪ መሐንዲስ II እና ረዳት መሐንዲስ VI

መ. ተባባሪ መሐንዲስ III እና ረዳት መሐንዲስ VII

ሠ. ምሩቅ ተባባሪ መሐንዲስ እና ረዳት መሐንዲስ II

29. በልዩ ሁኔታ የብቃት ማረጋጫ የምሥክር ወረቀት ስለመስጠት

1. ለረዥም ዓመታት የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ በውሃ ግንባታ ሥራ ላይ የቆየ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ያለው ሰው ከውሀ ጉድጓድ ቁፋሮና ጠረጋ ስራ በስተቀር በሌላ ስራ ተቋራጭነት ለመሰማራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ቢጠይቅ በዚህ መመሪያ እንዲሟሉ የሚጠየቁ መስፈርቶች ሳይጠየቅ፡-

ሀ. 10 ዓመት አገልግሎት ያለው ባለሙያ መሐንዲስ እንዲሁም 12 ዓመት አገልግሎት ያለው ተባባሪ መሐንዲስ የደረጃ 6 ሥራ ተቋራጭነት ምሥክር ወረቀት፣

Archive

ለ. 15 ዓመት አገልግሎት ያለው ረዳት መሐንዲስ የደረጃ 7 ሥራ ተቋራጭነት ምስክር ወረቀት፣ ማግኘት ይችላል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የምሥክር ወረቀት የተሰጣቸው ባለሙያዎች በሂደት ደረጃቸውን ከፍ ማድረግ ቢፈልጉ መመሪያው የሚጠይቀውን መሥፈርት ሙሉ በሙሉ ማሟላት ይጠበቅባቸዋል::

30. ስለአስፈላጊ መሣሪያዎች

1. የውሀ ነክ ሥራ ተቋራጮችን በተለያዩ ደረጃዎች ሊያስመድቡ የሚችሉ የመሣሪያዎች ዓይነት ብዛትና አቅም በዚህ መመሪያ ዕዝል 2 ላይ ሠንጠረዥ 6 መሠረት ይሆናል፣
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ለውሃ ነክ ሥራ ተቋራጭነት አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ባለቤት ካልሆነ መሣሪያዎቹን ለሶስት ወር በኪራይ ማግኘት የሚችል ስለመሆኑ በዚህ መመሪያ ዕዝል 2 ሠንጠረዥ 8 ላይ ለየደረጃዎቹ የተመለከተው ገንዘብ መጠን ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::
3. የተሟላ መሳሪያ የሌለው ተቋራጭ በሌሎች መሳሪያዎች መተካት የሚችለው በሠንጠረዥ 6.1 መሠረት ነው::
4. በሠንጠረዥ 6 እና በሠንጠረዥ 6.1 መሠረት መቅረብ ያልቻለ ከሆነ ለልዩነቱ መከራየት የሚያስችል አቅም ያለው ስለመሆኑ በዕዝል ሁለት ሠንጠረዥ ሰባት ላይ በተገለጸው መሠረት ከባንክ የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት::

31. የውሃ ነክ ሥራ ተቋራጮች የመሳሪያዎች ምደባ ፣አይነት፣ ብዛት፣ አቅምና ስለመሳሪያዎች መተካካት

1. ለተቋራጭ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች እንደአቅማቸውና እንደዋጋቸው በተለያዩ ማዕቀፎች ውስጥ ከባድ መሳሪያዎች፣መካከለኛ መሳሪያዎች፣ዝቅተኛ መሳሪያዎችና ቀላል መሳሪያዎች በመባል ይታወቃሉ::ሲጠቃለሉ እንደሚከተለው ነው::

   ሀ. ከባድ መሳሪያዎች የሚባሉት፣ዶዘር፣ክሬይን፣ ሎደር፣ ክሬሸር፣ ግሬደር፣ አክስካቬተርና መዳመጫዎች

   ለ. መካከለኛ መሳሪያዎች የሚባሉት፣ሚክሰር፣ ገልባጭ መኪናዎች ወይም ተመሳሳይ

   ሐ. ዝቅተኛ መሳሪያዎች የሚባሉት ፒክአፕ/ሲንግልና ደብል ካቢን/ ስቴሽን ዋገንና የመሳሰሉት

   መ. ቀላል የሚባሉት የቅየሳ መሳሪያዎችና ሌሎች የእጅ መሳሪያዎች ናቸው::

2. ስለሚተካኩ መሳሪያዎች

በተለያዩ ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው ውሃ ስራ ተቋራጭ በተለየ ሁኔታ ትርፍ መሳሪያዎች ወይም የተለዩ መሳሪያዎች ሲኖሩት ታሳቢ ተደርገው እንዲተካኩ ይደረጋል። በዚህ መነሻ;

Archive
Ministry of Water, Irrigation

ሀ. ከባድ መሳሪያ በትርፍነት ሲኖረው ለከባድ መሳሪያ ፣

ለ. መካከለኛ ሲኖረው ለመካከለኛ ወይም

ሐ. በትርፍነት ካለ በከባድ መሳሪያ፣

መ. እንደዚሁም ዝቅተኛ መሳሪያ በዝቅተኛ፣ ሊተካካ ይችላል።።ይህም ማለት

ሠ. ማንኛውም ከፍ ብሎ የሚታይ መሳሪያ ያለው አካል ዝቅ ብሎ ያለ መሳሪያ በሚያንስበት ወቅት ትልቁ ይተካታል ።።

ረ. ሆኖም ትንሽ መስለው የሚታዩት ትልቅ መስለው የሚታዩትን ሊተኩ አይችሉም።።

ዝርዝሩ ዕዝል 2 ሰንጠረዥ አምስት ላይ ታይቷል

ክፍል አምስት

የውሃ ነክ ሥራዎች ጥናት፣ ዲዛይን፣ ቁጥጥር ባለሞያዎችና አማካሪ ድርጅቶች ምዝገባ መስፈርት

(የንግድ ምዝገባ ኮድ 8839)

32. የአማካሪ ባለሙያዎች የሙያ ዝርዝር

በዚህ መመሪያ መሠረት በውሃ ጥናት፣ የዲዛይን ወይም ቁጥጥር የማማከር አገልግሎት ዘርፍ የሚሰማራ ባለሞያ ከሚከተሉት ሞያዎች በአንዱ ምሩቅ መሆን አለበት።።

1. ባለሞያ በውሃ ሀብት፣ በሃይድሮሊክስ፣ በመስኖና ድሬኔጅ፣ በውሃ አቅርቦት፣ በሳኒቴሪና ኢንቫይሮመንት፣ በሃይድሮፓወር፣ ሲቪል ኢንጂነር፣ ኤሌክትሮሜካኒካል መሃንዲስ፣ኢሌክትሪካል፣ሜካኒካል፣ በሃይድሮጂኦሎጂ ፣ኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ ወይም በሃይድሮሎጂ

2. በኢኮኖማክስ፣በሶሺኦሎጂ፣ በውሀ ጥራት፣ አግሮኖሚ፣ በአፈር ኤክስፐርት፣ በተቋም አደረጃጀትና አስተዳደር፣ ኤንቫይሮሜንት፣ ጂኦፊዚክስ፣በሕግ፣ በውሀ ሀብት፣በሃይድሮሎጂ፣ በእንሰሳት ሳይንስ፣ በሲቪል ኢንጂነሪንግ፣ በሃይድሮሊክስና በመሳሰሉት፣

3. ምሩቅ በኢኮኖሚክስ፣በሶሺኦሎጂ፣ በውሀ ጥራት፣ አግሮኖሚ፣ በአፈር፣ በተቋም አደረጃጀት፣ በአስተዳደር፣ ኤንቫይሮሜንት፣ ጂኦፊሲክስ፣ የውሀ ሕግ ባለሙያ ፣ሃይድሮሎጂ፣ በእንሰሳት ሳይንስ፣ በጂኦቴክኒክ፣ በሲቪል ኢንጂነር፣ በሃይድሮሊክስ፣ ኤሌክትሮሜካኒካል መሃንዲስ፣ ኢሌክትሪካል፣ሜካኒካልና በመሳሰሉት፣

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 - 4 በተጠቀሱት የሙያ መስኮች የተመረቁና የሚያስተምሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ከሚሰሩበት ተቋም መልቀቂያ ሳይጠየቁ የአማካሪነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

33. ስለባለሙያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራና የሞያ ልምድ

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 31 ላይ የተዘረዘሩት ምሩቅ ባለሞያዎች በዚህ መመሪያ በዕዝል ሶስት ሠንጠረዥ 9 ውስጥ የተመለከተው ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

34. የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ የሞያ መስኮች

1. የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ ሆኖ ለመመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርብባቸው የሞያ መስኮች የሚከተሉት ይሆናሉ፦

   ሀ. በውሃ ሀብትና ወይም በሃይድሮሊክስ ምሕንድስና፣
   ለ. በመስኖና ወይም በድሬኔጅ ምሕንድስና፣
   ሐ. በሃይድሮጂኦሎጂ
   መ. በመጠጥ ውሃና ፍሳሽ ምሕንድስና፣ በሳኒተሪ ምሕንድስና ወይም በኢንቫይሮሜታል ምሕንድስና፣
   ሠ. በሃይድሮፓወር ምሕንድስና፣
   ረ. በውሃ ጥራት ምህንድስና፣

2. የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ ምዝገባ አመልካቹ ያካበተውን የሥራ ልምድና አገልግሎት መሠረት በማድረግ የሞያ ደረጃ ዕውቅና የሚሰጥ በመሆኑ የምዝገባ መሥፈርቱን ለሚያሟሉ በመንግሥትም ሆነ በግል ድርጅት ለሚሠሩ ሁሉ የተፈቀደ ነው።

3. አመልካቹ የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ የምዝገባ ቅጽ በሚጠይቀው መሠረት ከትምህርቱና ከሥራ ልምዱ ጋር በተያያዘ በውሃ ነክ ሥራዎች ጥናት፣ ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ሥራዎች መሥራቱን የሚያረጋግጡ ሕጋዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት።

4. የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሙያ በዕዝል ሶስት ሠንጠረዥ 10 የተጠቀሱ ሪፖርቶችን ማቅረብ አለበት

35. የአማካሪ ድርጅት ሥራ መሪ ወይም ባለቤት ሆኖ ለመሠማራት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. የአማካሪ ድርጅት ሥራ መሪ ወይም ባለቤት ሆኖ ለመሥራት የሚፈልግ የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ በዚህ መመሪያ መሠረት ለመመዝገብና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት።

ሰነዶች ቤት
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ሀ. ወቅታዊ የሥራ መልቀቂያ ማረጋገጫ ወረቀት፣
ለ. ቢሮ፣ አስፈላጊ መሣሪያዎችና ፋሲሊቲዎች ስለመሟላቱ ማረጋገጫ፣
ሐ. ከሚመለከተው ክፍል የተሰጠ የንግድ መለያ ቁጥር፣
መ. ከሚያመለክትበት ሞያ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የትምህርት ማስረጃ ፎቶ ኮፒ፣
ሠ. በዚህ መመሪያ በዕዝል 3 ሠንጠረዥ 9 ላይ በተመለከተው መሠረት ወይም ከምረቃ በኋላ በጠየቀበት የሥራ መስክ በሞያው መሥራቱን የሚያረጋግጥ የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ /ለ/ እና /ሐ/ ላይ የተመለከቱት የረዥም ጊዜ ባለልምድ ባለሞያ መስፈርቶች ለድርጅት ባለቤትነት ባላመለከቱ ባለሞያዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

36. ስለ አማካሪ ድርጅቶች ምዝገባ

1. ማንኛውም በውሃው ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ የሚሠማራ ድርጅት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምድቦች በአንዱ ለመመዝገብ ሊያመለክት ይችላል፦

ሀ. በአጠቃላይ የውሃ ሀብት አማካሪነት፣
ለ.በመጠጥ ውሃና ፍሳሽና /ወይም ሳኒተሪ/ኢንቫይሮሜንታል ምሕንድስና አማካሪነት፣
ሐ. በሃይድሮ ፓወር ምሕንድስና አማካሪነት፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከ/ሀ/ - /ሐ/ በተዘረዘሩት የማማከር አገልግሎት ዘርፎች የተመዘገቡ ድርጅቶች በተመዘገቡበት ምድብና የማማከር አገልግሎት ዘርፍ የጥናት፣ ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ተግባራት ለማከናወን ይችላሉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር እንዲውል በሚኒስቴሩ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት መሆን አለበት።

37. የአማካሪ ድርጅቶች ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት

1. የአማካሪ ድርጅቶች ደረጃ በዚህ መመሪያ በዕዝል 3 ከሠንጠረዥ 11-13 በተዘረዘሩት የመመዘኛ መሥፈርቶች መሠረት የሚወሰን ይሆናል።
2. አንድ የአማካሪ ድርጅት ደረጃዎቹ የሚጠይቁትን መሳሪያዎችና ሌሎች መስፈርቶች አስካሟላ ድረስ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ከዝቅተኛ የአማካሪነት ደረጃ ወደ ቀጣይ ከፍተኛ የአማካሪነት ደረጃ ለማደግ ይችላል።

Archive

38. ለከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የአቅም ግንባታ አማካሪነት ዝቅተኛ የምዝገባ መስፈርት

ለከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የአቅም ግንባታ አማካሪነት አማካሪ ድርጅቱ የከተማ ውሃ ቦርድ ልማት ስፔሻሊስት፣ ቢዝነስ ፕላኒንግ ስፔሻሊስት፣ ሳኒቴሽን ስፔሻሊስትና ቴክኒካል ስፔሻሊስት ያካተተ መሆን አለበት:: እነሱም የሚከተሉትን ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ማሟላት ይገባቸዋል::

1. የከተማ ውሃ ቦርድ ልማት ስፔሻሊስት

የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ በማኔጅመንት፣ በምሕንድስና፣ በተዛማጅ የቴክኒክ ሞያ የሆነና ቢያንስ ሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው:: ይህም ልምድ በከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ቢሆን ይመረጣል::

2. ቢዝነስ ፕላኒንግ ስፔሻሊስት

የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ በኢኮኖሚክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በተዛማጅ ሞያ የሆነና ቢያንስ አንድ ዓመት የሥራ ልምድ በሂሣብ ትንተናና ቢዝነስ ፕላኒንግ::

3. ሳኒቴሽን ስፔሻሊስት

የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ፣ ዲፕሎማ በኅብረተሰብ ጤና አጠባበቅ፣ ሳኒቴሽን፣ ወይም በተዛማጅ ሞያ የሆነና ቢያንስ አንድ ዓመት የሥራ ልምድ ያለው:: ይህም ልምድ በከተሞች ሳኒቴሽንና ፕላኒንግ ቢሆን ይመረጣል::

4. ቴክኒካል ስፔሻሊስት

የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ፣ ዲፕሎማ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ወይም በተዛማጅ የቴክኒክ ሞያ የሆነና ቢያንስ ሁለት ዓመት በከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዲዛይን፣ ኦፕሬሽንና የኮንትራት አስተዳደር የሥራ ልምድ ያለው::

39. የወረዳ ዋሽ አማካሪ ዝቅተኛ የምዝገባ መስፈርት

የውሀ አቅርቦት መሀንዲስ፤ ሀይድሮጂኦሎጂስት የአካባቢ ሳኒቴሽንና የሀይጅን ኤክስፐርትና የህብረተሰብ ልማት እስፔሻሊስት ያካተተ መሆን አለበት::ዝቀተኛ የትምህርትና የስራ ልምዳቸው የሚቀጥለው ነው::

1. የውሀ አቅርቦት መሀንዲስ

   የትምህርት ደረጃ ዲግሪ በውሀ አቅርቦት ወይም በውሀ ሀብት ወይም በውሀ ሀብት ሲቪል ምህንድስና ወይም በተዛማጅ መስክ የሆነና በመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ 7ዓመት፤ በሁለተኛ

መዝገብ ቤት
Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ዲግሪ 5 ዓመት ወይም በሶስተኛ ዲግሪ 3ዓመት በውሀ አቅርቦት ጥናት፣ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥርና አስተዳደር የስራ ልምድ ያለው

2. ሀይድሮጂኦሎጂስት
   የትምህርት ደረጃ ዲግሪ በሀይድሮሎጂ በጂኦሎጂ ወይም በተዛማጅ መስክ የሆነና በመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ 7ዓመት፤ በሁለተኛ ዲግሪ 5ዓመት ወይም በሶስተኛ ዲግሪ 3ዓመት በሀይድሮሎጂካል ጥናትና፣ዲዛይን የስራ ልምድ ያለው
3. የአካባቢ ሳኒቴሽንና ሀይጅን ኤክስፐርት
   የትምህርት ደረጃ ዲግሪ በሳኒተሪ፣ በህዝብ ጤና በአካባቢ ጤና ወይም በተዛማጅ መስክ የሆነና በመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ 7ዓመት፤ በሁለተኛ ዲግሪ 5ዓመት ወይም በሶስተኛ ዲግሪ 3 ዓመት በአካባቢ ሳኒቴሽንና ሀይጅን የስራ ልምድ ያለው
4. የህብረተሰብ ልማት እስፔሻሊስት
   የትምህርት ደረጃ ዲግሪ በሶሽዮሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ ወይም በዴቨሎፕመንት ጥናቶች የሆነና በመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ 7ዓመት፤ በሁለተኛ ዲግሪ 5ዓመት ወይም በሶስተኛ ዲግሪ 3 ዓመት የስራ ልምድ ኖሮት ጥሩ የማቀድና የኮሙኒኬሽን ችሎታና የስራ ልምድ ያለው

ክፍል ስድስት

የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ባለሙያና የሥራ ተቋራጭ የምዝገባ መስፈርት

(የንግድ ምዝገባ ኮድ 5022)

40. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ባለሞያዎች ዝርዝር

በዚህ መመሪያ መሠረት በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ጠረጋ የሥራ ዘርፍ የሚሠማራ ሥራ ተቋራጭ የሚከተሉት ባለሞያዎች ሊኖሩት ይገባል::

1. ጂኦሎጂስት፣ ጁኒየር ሃይድሮጂኦሎጂስት፣ ሲኒየር ሃይድሮጂኦሎጂስት፣
2. የቁፋሮ ተቆጣጣሪ፣
3. ዋና ቆፋሪ፣
4. ቆፋሪ፣
5. ረዳት ቆፋሪ፣

41. ስለ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 39 ላይ የተዘረዘሩት ባለሞያዎች በዚህ መመሪያ በዕዝል አራት ሠንጠረዥ 14 ውስጥ የተመለከተው ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

42. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የምደባ መሥፈርቶች

1. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ስምንት ደረጃዎች ይኖሩታል።
2. የሥራ ተቋራጮች ደረጃ አወሳሰንም፦
   ሀ. በግንባታ ዋጋ፣
   ለ. በባለሞያዎች ስብጥር፣ የሥራ ልምድና የሞያ ብቃት፣
   ሐ. በመሣሪያዎች ዓይነት፣ አቅምና ብዛት፣
   መ. በቢሮ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

43. የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የግንባታ ዋጋ መሥፈርት

የግንባታ ዋጋን መሠረት ያደረገ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት በዚህ መመሪያ በዕዝል አራት በሠንጠረዥ 15 በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

44. የጉድጓድ ቁፋሮ የሥራ ተቋራጮች የባለሞያዎች ስብጥር፣ የሥራ ልምድና የሞያ ብቃት መስፈርት

የባለሞያዎች ስብጥርን፣ የሥራ ልምድና የሞያ ብቃትን መሰረት ያደረገ የጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታ እና ጠረጋ የሥራ ተቋራጮች ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት በዚህ መመሪያ በዕዝል አራት ከሠንጠረዥ 16 እስከ 17 በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡

45. አስፈላጊ መሣሪያዎች

1. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግምባታ እና ጠረጋ ሥራ ተቋራጮችን በተለያዩ ደረጃዎች ሊያስመድቡ የሚችሉ የመሣሪያዎች ዓይነት፣ ብዛት እና አቅም በዚህ መመሪያ በዕዝል አራት ሠንጠረዥ 19 በተመለከተው መሠረት ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ለጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭነት አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ባለቤት ካልሆነ መሣሪያዎቹን ለሶስት ወር በኪራይ ማግኘት የሚችል ስለመሆኑ በዚህ መመሪያ በዕዝል አራት ሠንጠረዥ 20 ላይ ለየደረጃዎቹ የተመለከተው ገንዘብ በድርጅቱ ስም በባንክ ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከተሰጠ 15 ቀናት ያላለፉት የባንክ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት።
3. ማንኛውም የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭ ደረጃው የሚጠይቀውን መሳሪያና ሌሎች መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ ያለ ምንም ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ከገዘቱተኛ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጭነት ደረጃ ወደ ቀጣይ ከፍተኛ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታና ጠረጋ ሥራ ተቋራጮች ደረጃ ማደግ ይችላል።

Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ክፍል ሰባት

የሳኒቴሪ ባለሙያና የሳኒቴሪ ሥራ ተቋራጭ የምዝገባ መስፈርት (የንግድ ምዝገባ ኮድ 5034)

46. የሳኒቴሪ ባለሞያዎች ዝርዝር

በመስኩ የሚሰማሩ ባለሙያዎች በቴክኒሻንነት፤በረዳት ምህንድስና፤ተባባሪ ምህንድስና፤ሳኒቴሪ ምህንድስና፤ በምህንድስና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች፤ ከኮሌጆች፤ከዩንቨርሲቲዎች የተመረቁ መሆን አለባቸው።የሳኒቴሪ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በዕዝል ስድስት ሠንጠረዥ 24 መሠረት ይሆናል

47. የውሃ የሳኒታሪ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የምደባ መሥፈርቶች

1. በሣኒቴሪ ሥራዎች ተቋራጭነት የሚሰማራ ሰው የሚስተናገደው ባለው የትምህርት ዝግጅትና ስራ ልምድ መነሻ ነው።

2. በዚህ መመሪያ ሳኒቴሪ ስራ ተቋራጮች ደረጃ 6፤7፤8፤9 ሆነው እንደሚመደቡ ታሳቢ ተደርጓል ።

3. በቀድሞው መመሪያ ደረጃ አንድ እስከ አራት በሚል ተመድበው ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው የነበሩት በዚህ መመሪያ መሰረት እንደሚያሟሉት ደረጃ በአዲስ መልክ ደረጃ 6፤7፤8፤9፤10 ተደርገው ይመደባሉ።

4. በሣኒቴሪ ሥራዎች ተቋራጭነት የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ለደረጃው የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ በዕዝል ስድስት ሠንጠረዥ 25 መሠረት ማሟላት አለበት።

5. በሳኒቴሪ ስራ ተቋራጭነት ለመሰማራት ያመለከተ ሰው ዕቃዎችና መሳሪያዎች ያሉት ስለመሆኑ ሳይጠየቅ ይስተናገዳል።

48. የውሃ የሳኒታሪ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የግንባታ ዋጋ መሥፈርት

የግንባታ ዋጋን መሠረት ያደረገ የሳኒታሪ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ አወሳሰን መሥፈርት በዚህ መመሪያ በዕዝል ስድስት በሠንጠረዥ 27 በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ

49. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስትሩ ሊሻሻል ይችላል።

50. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ነሃሴ 01 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሞቱማ መቃሳ
የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር * The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Water, Irrigation & Electricity

ዕዝል

Ministry of Water, Irrigation & E

ዕዝል አንድ

ሠንጠረዥ አንድ

የውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ ባለሞያዎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሞያ ልምድ

1. **ባለሞያ መሐንዲስ/ Professional Engineer/**

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተቋም የቢ.ኤስ.ሲ. ዲግሪ ወይም ከዛ በላይ	ከምረቃ በኋላ ከ5 ዓመት በላይ

2. **ምሩቅ መሐንዲስ/ Graduate Engineer/**

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተቋም የቢ.ኤስ.ሲ. ዲግሪ ወይም ከዛ በላይ	0 - 5 ዓመት

3. **ተባባሪ መሐንዲስ/ Associate Engineer/**

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተቋም ዲፕሎማ	ከምረቃ በኋላ ከ5 ዓመት ያላነሰ

4. **ተመራቂ ተባባሪ መሐንዲስ/ Graduate Associate Engineer/**

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተመሳሳይ ተቋም በውሃ ቴክኖሎጂ ምሕንድስና ዲፕሎማ	0 - 5 ዓመት

1. **ረዳት መሐንዲስ/ Engineer Aide/**

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
ከታወቀ ቴክኒክ ት/ቤት /10+2, 12+2, 10+3, 12+3) (Level - 2, Level - 3)	ከምረቃ በኋላ ከ5 ዓመት ያላነሰ

Archive
Ministry of Water, Irrigation & Electricity

6. ምሩቅ ረዳት መሐንዲስ/Graduate Engineer Aide/

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
ከታወቀ ቴክኒክ ት/ቤት /10+2, 12+2, 10+3, 12+3) (Level - 2, Level - 3)	0 - 5 ዓመት

7. ምሩቅ ምህንድስና ነክ ቴክኒሺያን

የትምህት ደረጃ	የሥራ ልምድ
